# አንተ ቀሥተ ደመና፤ በቅሊንጦ እስር ቤት (ነሐሴ 28 ቀን 2008)

 *

“ቀስቴን በደመና አድርጌአለሁ፥ የቃል ኪዳኑም ምልክት…  እግዚአብሔርም ኖኅን፦ በእኔና በምድር ላይ በሚኖር ሥጋ ባለው ሁሉ መካከል ያቆምሁት የቃል ኪዳን ምልክት ይህ ነው አለው።” (ዘፍጥረት 9፡13 & 17)

አለም አረገደ መሥካሪ ፍሊጋ፣

የቅሊንጦ እሥር ቤት ቅዳሜ ሲቃጠል፤ (September 3, 2016)

አንተ  ቀሥተ ደመና

ከዚያ በመገኘት፣ ሁሉን የመዘገብህ፣

እባክህ ንገረኝ  በሞቴ ጭጭ አትበል።

ለምን አሥረገደን

ማን እንዳቃጠለው ምሥክር ፍሊጋ

አትሞት የለም ወይ በቀሥተ ደመና

አንድ አምላክ እግዜአብሔር፤

መሐላን ጠባቂ ለኢትዮጵያ ምድር።

በቅሊንጦ እስር ቤት

በኢትዮጵያ ባንዴራ አስመሥሎ ሣለህ

አንተ ቀሥተ ደመና፤

አምላክ ቃል ኪዳኑን መቸ እረሳና።

ሐቅን ሳረጋግጥ በሰው አካልነት፤

ከቅሊንጦ እስር ቤት፤

እስኪ ማንን ልጥራ በቀለ ገርባን፣

ወይስ የሙብት ተሟጋቹ ዮናታን ተስፋዬን፤

ጌታቸው ሽፈራው ሌላም ብዞች አሉ

እነማን ነበሩ ላአለፈውም ቢሆን?

በአምቦ፣ በአንጎበር፤

በዚያ ደብረታቦር

በቃሊቲም መንደር።

መጠየቅ ይገባል

ኃይለማርያም ደሳለኝ ጠ/ሚንስትሩን ጭምር፤

ተለማምደው እንደሁ እውነቱን መናገር።

እስኪ አጠያይቁ ጠበንጃ አነሰ ወይ

በቅሊንጦ እስር ቤት፣

እንደ ጃርት አራዊት፤

በመርዘኛው ጭሱ አፍኖ የሚገድል

በአጋዜ ባዙቃም ማን አለብኝ ብሎ የሚሸልል።

ወይንም በየሱስ አረ ባለህ በሉ፤

የኢትዮጵያ ልጆች እስከመቸ ድርስ

እንዲህ ይቃጠሉ!!!

ጧት አልጸለየም ወይ  ያነ ኃይለምርያም፤

ጸጋውን ረስቶ፣ ለመንፃት ፈለገ በውገኖቹ ደም።

አለም አረገደ መሥካሪ ፍለጋ፣

የቅሊንጦ እሥር ቤት ቅዳሜ ሲቃጠል፤

አንተ  ቀሥተ ደመና

ከዚያ በመገኘት፣ ሁሉን የመዘገብህ፣

እባክህ ንገረኝ  በሞቴ ጭጭ አትበል።

አንተ ቅስተ ዳመና እስኪ ልጠይቅህ

ማን ነበር አቃጣይ፤

ጥይት ያንሳል ብሎ በሳት ፍም የሚያጋይ።

© ለመለም ፀጋው , September 4, 2016

በቅሊንጦ በአምቦ፣ በጎንደር፣ በደብረ ታቦር፣ በአንጎበር (ባህታ እሥር ቤት)ና በቃሊቲ ለተቃጠሉ እስረኞች መተሰቢያ የተጻፈ

* photo from http://www.ethiopanorama.com/?p=38483 (September 3, 2016)